በነጻ የሚታደል

ቤርያ



የመንፈሳዊ ትምህርት ጋዜጣ ቁጥር ፲፩

እነዚህም [የቤርያ ሰዎች] በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፡- ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው እለት እለት መጻህፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ (ሐዋ ፲፯፡ ፲፩)፡፡

የህይወት ትምህርት ከኋሪዎቹ

አንድ ፎቶ ኮፒ ቤት እንዲህ የሚል ፖስተር አነበብኩ፡- "እግዚአብሄር ሆይ... ደግ እንደአብርሃም፣ ታዛዥ እንደይስሃቅ፣ የዋህ እንደዮሴፍ፣ ቅን እንደሙሴ፣ ትእግስት እንደኢዮብ፣ ምስጋና እንደዳዊት፣ ጥበብ እንደሰሎሞን፣ እምነት እንደዳንኤል፣ ትህትና እንደጴጥሮስ፣ ሰባኪ እንደጳውሎስ፣... ታደርግልኝ ዘንድ እማጸንሃለሁ፡፡" በዚህ ፖስተር ላይ ጸሃፊው ስለጥቂት የመጽሀፍ ቅዱስ ሰዎች እሱ የወደዳቸውን አንዳንድ ባህሪዎቻቸውን መርጦ ጽፏል፡፡ ይህን ማድረጉ ክፋት የለውም፡፡ ነገር ግን የነዚህ ሰዎች ባህሪ ይህ ብቻ ነው? ሌሎችስ እነዚህ ተግባራትና ባህሪዎች እንዲያውም በበለጠ መልኩ ያሏቸው ሰዎች በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የሉም ማለት ነው?

አንዳንድ የመጽሃፍ ቅዱስ ሰዎችን መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጹበት የተሟላ ባህሪያቸውና ድርጊታቸው አናውቃቸውም፡፡ አንዳንድ ባህሪዎቻቸውንና ድርጊቶቻቸውን አጋንነን ትልቅ ትምህርት የምናገኝባቸውን ሌሎቹን መገለጫዎቻቸውን ፈጽሞ እንረሳቸዋለን፡፡ እንዲሁም መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለነሱ ተጨማሪ ማብራሪያ ስላልተሰጠ እኛም በተሳሳተ መንገድ የተረዳናቸው ሰዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ በተጨማሪ የአንዳንድ ሰዎች ታሪክ ቁልጭ ብሎ ተጽፎ እያለ ከጀርባው ያለውን ትርጉም በንባባችንም ሆነ በስብከታችን ቸል ብለነው ትልቅ ትምህርት ሳንገበይ ቀርተናል፡፡ እነዚህ ሰዎች እነማናቸው? ትኩረት የተነፈገው ታሪካቸው፣ ንግግራቸው፣ ባህሪያቸውና ድርጊታቸውስ? ከነዚህ ሰዎች መካከል ስለጥቂቱ ቀጥለው ያንብቡ፡፡

ሐዋርያው ቶማስ

ቶማስ የሚታወቀው በተጠራጣሪነቱ ነው፡፡ ተጠራጣሪነቱ እውነት ቢሆንም ደፋርነቱ ግን ፈጽሞ ተረስቷል፡፡ ኢየሱስ አልአዛርን ከሞት ለማስነሳት ወደቢታንያ እንደሚሄዱ ሲናገር ሌሎቹ ደቀመዛሙርት ካሁን በፊት አይሁድ በይሁዳ ሊወግሩት እንደፈለጉት በማውሳት ኢየሱስ እንዳይሄድ ሲመክሩት ቶማስ ግን ሄደን አብረን ከጌታ ጋር እንሙት ብሎ ሌሎቹንም አብረውት እንዲሄዱ አነሳሳ፡፡ ይህ የሚነግረን ከጌታ ጋር እስከሞት ድረስ አብሮ ለመሄድ ያለውን ድፍረት ነው (ዮህ ፲፩፡5-16)፡፡ እንዲያውም በድፍረቱ ከጴጥሮስ የተሻለ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ከጌታ ጋር አብሮ ለመሞት ምሎ ተገዝቶ ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ጌታን አላውቀውም ብሎ ሲክድ (ማቴ 26፡33-35፣ 69-75) ቶማስ ግን ይህን አላደረገም፡፡ ስለዚህ እኛም እስከሞት ድረስ ለጌታ ዋጋ ለመክፈል መድፈርን ከቶማስ እንማር፡፡

የአስቆሮቱ ይሁዳ

ይሁዳ ለገንዘብ የተገዛ ሰው ስለመሆኑ እና በገንዘብ ፍላጎቱ በመታወሩ ምክንያት በጭካኔ ንጹሁን ጌታ አሳልፎ ስለመስጠቱ በተደጋጋሚ ይሰበካል፡፡ ነገር ግን ሰባኪዎች በግልጽ የማያብራሯቸው ከይሁዳ ተግባራትና ለሐዋርያነት መመረጥ ጋር የተያያዙ እና በዚህ ጽሁፍ ልንማራቸው የሚገቡ ሁለት ጉዳዮች አሉ፡፡

ለመነሻ በይሁዳ ተግባር በኩል ያለውን የሚመለከቱ ሁለት ጥያቄዎችን ልጠይቅ፡፡ አንደኛ ጌታን እንደሚከድ እየተነገረውና "የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት" የተባለውን እየሰማ፣ እንዲያውም "ሂድ ፍጠን የምታደርገውን አድርግ" እየተባለ ቆም ብሎ ጌታን አሳልፎ

የመስጠት ሃሳቡን ለመከለስ ያልቻለው ለምንድነው (ማቴ 26፡21-15፤ ዮሀ 13፡21-27)? ሁለተኛ ጌታ ብዙ ምስጢሮችን ሲገልጥ እያየው እሱም ለአገልግሎት ከተሰበሰበው ገንዘብ ሲሰርቅ እንደሚያውቅበት እንዴት ማሰብ አቃተው (ዮሀ 12፡3-6)? እናንተም እንደእኔ እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ ብየ አስባለሁ፡፡ ታዲያ እነዚህን ነገሮች አለማሰቡ አስገራሚ አልሆነባችሁም?

ይሁዳ እነዚህን ነገሮች ማገናዘብ ያልቻለው ሃሳቡ በገንዘብ ፍቅር ስለተያዘና የሚያስበው ገንዘቡን ማግኘቱን ብቻ እንጂ ገንዘቡን የሚያገኝበትን መንገድ ጤናማነት ስላልነበረ ነው፡፡ ጌታ ስለሃሳቡና ስለስራው ማወቅ አለማወቅ ማሰብ ለሱ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ዋናው ነገር ገንዘቡን የሚያገኝበትን መንገድ ጌታ አለመዝጋቱ ብቻ ነው፡፡

እኛም ለአንድ ነገር ከመጠን በላይ ከተገዛን እንደይሁዳ ለሌሎች ነገሮች እንደምንታወር ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚህ እንደይሁዳ ከማንወጣበት አዘቅት ውስጥ እንዳንገባ ከጌታ ውጭ ማንኛውንም ነገር ከመጠን በላይ ከመውደድ ልንታቀብ ያስፈልጋል፡፡ አንድን ነገር የምንወድበትን ደረጃ ከመጠን እንዳያልፍ ሁልጊዜም ልንመዝነው ድንገት አምልጦን ካለፈ ደግሞ ፈጥነን ልናስተካክለው ይገባናል፡፡

ለሐዋርያነት በመመረጡ በኩል ደግሞ አስገራሚ የሆነውና ሲነሳ ያላሁት ጉዳይ አሳልፎ እንደሚሰጠው እያወቀ ኢየሱስ እሱን ከሐዋርያቱ ጋር መቀላቀሉ ነው፡፡ ሰው እንዴት የሚጎዳውን ያቀርባል? እንዴትስ የማይገባውን የሐዋርያነት ማእረግ ይሰጠዋል?

ወደእውነቱ ስንመጣ ጌታን የመካድና አሳልፎ የመስጠት ስራዎች የሐጢያት ተግባራት ስለሆኑ በቅዱሳን አይሰሩም፡፡ ስለዚህ ለዚህ ስራ የሚመጥን ማለትም ወደመዳን የማይመጣ፣ የስጋ ፍላጎቱን ብቻ የሚያዳምጥ እና በተመሳሳይ ተግባሩ የሚታወቅ ሰው ስላስፈለገ ኢየሱስ ይሁዳን ጠራው፡፡ ዛሬም ይሁዳ ጌታ እንዲሰቀል ሁኔታዎችን በማመቻቸት የማዳን ስራውን እንዳስፈጸመ ሁሉ አንዳንድ ሰዎች እኛ ባይገባንም በጠማማነታቸው የሚፈጽሙት የእግዚአብሄር ዓላማ አለ፡፡ ለምን ወደእግዚአብሄር ቤት እንደሚመጡ የሚገርመን፣ እንደገና መወለዳቸውን እንኳን የምንጠራጠረው፣ ተምረውና ተመክረው የማይለወጡ፣ ክፉት የሞላባቸው ብሎም ሁሌም የጠብና የብጥብጥ ምንጮች የሆኑ ሰዎች በቤተክርስቲያን አሉ፡፡ መኖራቸው ሲገርመን ሽማግሌ፣ መጋቢ፣ ወዘተ ሊሆኑ ወይም ሌሎች ወሳኝ የአገልግሎት ቦታዎች ላይ ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ፈጽሞ ለአገልግሎት አልመናቸው የማናውቅ ሰዎች ከመረዳታችንና ከአቅማችን በላይ በሆነ ምክንያት ወደአገልግሎት ቢመጡ ሊደንቀን አይገባም፡፡ ተፈልገው ሊሆን ስለሚችል ዝም እንበል፡፡

ቃየን

የቃየን መስዋዕት በእግዚአብሄር ሞገስ ያጣበት ምክንያት በእርግጠኝነት ምንድነው (ዘፍ 4፡3-7)? ብዙዎች እንደሚሰብኩት የእምነት ችግር ነው? ዕብ 11፡4 ይህን ይደግፋልን? በፍጹም፡፡ ዋናው ችግሩ ያቀረበው መስዋዕት ደረጃ ሲሆን የደረጃው ልዩነት የተከሰተው ደግሞ በአመራረጥ ሂደቱ ምክንያት ነው፡፡ አቤል ከስራው ውጤት በኩራቱን ከበኩራቱም ስቡን ሲያቀርብ ቃየን ግን ከምድር ፍሬ መሃል ማንኛውንም እጁ እንዳመጣለት ቆንጥሮ አቀረበ፡፡ በመስዋእቱ አመራረጥ አማካይነት እግዚአብሄርን ማክበር፣ መውደድና ማምለክ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሄር መገዛት በልቡ ውስጥ እንደሌለ አንጸባረቀ፡፡ በዚያ ምክንያት እግዚአብሄር ወደመስዋእቱ እንዳልተመለከተ ሲገነዘብ ደግሞ በአቤል በመቅናት ወደሌላ እርምጃ ማለትም ወደመግደል በመሻገር ለእግዚአብሄር ያለውን ንቀት ገለጠ (ዘፍ 4፡5-8)፡፡

መስዋእት ባያቀርብ ኖሮ ግን ከእግዚአብሄር ጋር ባልተጣላ እንዲሁም ለሌላው ለከፋው ኃጢያት ባልተጋለጠም ነበር፡፡ በእግዚአብሄር ፊት ሞገስ ለማግኘት መስዋዕት ማቅረብ ግድ አይደለም፡፡ ቃየን መስዋዕት ማቅረቡ ቀርቶ ልቡ እግዚአብሄርን በማክበር ቢሞላ ኖሮ ግን እግዚአብሄር እንደሱ የሚወደው ሰው አይኖርም ነበር፡፡

እኛም ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሄር ስናደርግ ከልብ አስበንበትና በፍጹም ደስታ እናድርግ፡፡ የልብ ዝግጅታችን አነስተኛ ከሆነ ወይም ደስታ በውስጣችን ከሌለ ያሰብነውን ባናደርገው የተሻለ ነው፡፡ ካለደረጋችሁ ብሎ የሚያስገድደን የለም፡፡ ከውስጣችን በመጣ ፍላጎት ሳይሆን ለይስሙላና

ከሌሎች ላለመለየት ስናደርግ በአደራረግ ሁኔታችን የልባችን ሃሳብ ይገለጥና ሌሎች ያላሰብናቸው ተጨማሪ ችግሮች ውስጥ እንገባለን::

የፈርኦን የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ

ብዙ ሰባኪዎች ስለፈርኦን ጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ሲሰብኩ ዮሴፍ በተረጎመለት ህልም መሰረት ከእስር ሲፈታ ስለዮሴፍ ተሰርቆ መምጣትና በግፍ መታሰር ለፈርኦን ነግሮለት እሱንም እንዲያስፈታው ዮሴፍ አደራ በማለቱ ነገር ግን የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ዮሴፍን በመርሳቱና ውለታ ቢስ በመሆኑ ላይ ያተኩራሉ (ዘፍ 40፡13-15፣23):: በርግጥ ይህ እውነት መሆኑን አንክድም:: ነገር ግን እውነቱ ይህ ብቻ አይደለም:: የጠጅ አሳላፊዎቹን አለቃ በግማሽ ታሪክ መገመት ትክክል አይደለም:: ሚዛናዊ መሆን ይገባናል::

ብዙዎቻችን ስለጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ስናስብ አራት ነገሮችን እንዘነጋለን::

ሀ. ለመሆኑ ወዲያው እንደተፈታና ወደስራ ቦታው እንደተመለሰ ዮሴፍን ቢያስታውስስ ኖሮ የእግዚአብሄር ጊዜ ሳይደርስ ዮሴፍ ይወጣል ብለን እናስባለን? ስንት ዘመድና አለ የተባለ አማላጅ ሁሉ ለፍቶልን እግዚአብሄር ስላልፈቀደ ብቻ ጉዳዮቻችን ሳይፈጸሙ የቀሩ ስንቶች ነን? ጊዜው ሲደርስ ግን እግዚአብሄር የማንጠብቀውን ሰው አስነስቶ ነገሮቻችንን ያከናወነውስ ስንት ጊዜ ነው? ስለዚህ የጠጅ አሳላፊውን ዮሴፍን መርሳት ከእግዚአብሄር ጊዜ ጋር አገናኝተን ልንተረጉመው ይገባል እንጂ የሰውየው ጥፋት ብቻ አድርገን ልንወስደው አይገባም ::

ለ. በኋላስ ቢሆን ፈርኦን ህልም የሚፈታለት ሲፈልግ ይህ ጠጅ አሳላፊ ዮሴፍ መኖሩን ባያስታውስ ኖሮ ዮሴፍ እንደታሰረ ይቀር አልነበረምን? እግዚአብሄር ለዚህ ቀን ያስቀመጠው የዮሴፍ ወኪል አድርገን ብንቆጥረው እንሳሳታለን ብላችሁ ታስባላችሁ? አንሳሳትም:: ዮሴፍም ቢጠየቅ ከኛ በተቃራኒው ይህ ሰው ትልቅ ባለውለታው እንደሆነ እንደሚነግረንና በስልጣን ዘመኑ ሁሉ በጥሩ አይን እንደሚያየው እርገጣ ሁኑ::

ሐ. ይህ ሰው ስለዮሴፍ ለፈርዖን ቢነግር እንኳን ፈርኦን ስለአንድ እብራዊ ቆርቁሮት ያስፈታዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ከዮሴፍ ይልቅ ከሳሾቹን ግብጻውያን የበለጠ እንደሚሰማ አትጠራጠሩ::

መ. ዮሴፍ ግብጽ የመጣው በባርነት እንጂ ለመምጣት ፈልጎ ስላልሆነ በዚህ መንገድ ከእስር ቤት ቢወጣ ወዲያውኑ በቀጥታ ወደአገሩ እንደሚመለስ አስባችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሄር ግን በግብጽ አገር ያሰበለት ነገር ስላለ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ዝም አለው:: ዮሴፍ በግብጽ ታሪክ ውስጥ አሻራውን የሚያስቀምጥበት ወቅት እስኪደርስ ጠጅ አሳላፊው እንዲረሳው አደረገው::

ለእግዚአብሄር ሰዎች አለም እንድታስብና እንድታዝን መጠበቅ ሞኝነት ነው:: የእግዚአብሄር ሰው የእግዚአብሄር እቃ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በህይወቱ የሚከናወነው ሁሉ ባለቤቱ እግዚአብሄር ያቀደለት ብቻ ስለሆነ አይቻልም ባለበት ሁኔታ እንኳን ሊሆንለት፣ ይቻላል ባለበት ሁኔታ ደግሞ ላይሆንለት ይችላል:: የእግዚአብሄር ፈቃድ ካልሆነ በእግዚአብሄር ሰው ላይ ጥሩ የተባለ ሰው ይከፋበታል፤ ጊዜው ከደረሰ ግን ክፉ የተባለው እንኳን የመጨረሻ ደግ ሆኖ ይቀየርለታል:: እግዚአብሄር ሲያዝዝ ንፉጉ ቸር ሲሆለት፣ እግዚአብሄር ካላዘዘ ደግሞ ቸሩ ንፉግ ይሆንበታል:: በሁላችን የሚሆነው ይኸው ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሄርን ጊዜ መጠበቅ፣ ይሆንልናል ብለን ጠብቀን የማይሆንልን ሁሉ የጌታ ፈቃድ ስላልሆነ እና ጊዜው ስላልደረሰ እንደሆነ በመረዳት ሰውን ከመቀየም መጠበቅ እና ለተሻለው የእግዚአብሄር ጊዜ እየተዘጋጀን መቆየት ይኖርብናል::

አልጋውን ተሸክሞ የሄደው ሰው

በአልጋ ወደኢየሱስ መጥቶ ተፈውሶ አልጋውን ተሸክሞ ስለሄደው ሰው ሲሰበክ ስላመጡት ሰዎች እምነት እና ስለኢየሱስ ፈዋሽነት ረገጥ ተደርጎ ይነገራል (ማቴ 9፡2-7፤ ማር 2፡1-12):: ነገር ግን ከፈውሱ በኋላ ስለሆነው ነገርና ስለሚሰጠው ትምህርት ሲነገር አልሰማሁም:: ከዚህ ከተፈወሰው ሰው ድርጊት ጀርባ እስካሁን ያላስተዋልናቸው ሁለት እውነታዎች አሉ::

ሀ. ተሸካሚዎቹ በሽተኛውን ተሸክመው የመጡት በአልጋ

ነው፡፡ በሽተኛው ከተፈወሰ በኋላ በእግሩ መሄድ ስለሚችል ሲመለሱ የሚሸከሙት አልጋውን ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን የተፈወሰው ሰው አልጋውንም ከመሸከምም ገላገላቸው፤ ራሱ ተሸከመው፡፡ በሌላ አነጋገር ሰውየውና አልጋው ርስ በርሳቸው ተሸካከመው ሄዱ፡፡ ሰውየው ከዕዳነት ተሻግሮ ራሱን መቻሉ ብቻ ሳያበቃ መፍትሄ መሆንም ጀመረ፡፡

ይህ ሰው ጌታ ካደረገለት የተነሳ ከእዳነት ተሻግሮ ራሱን መቻሉ ብቻ ሳያበቃ መፍትሄም እንደሆነ ሁሉ ወደጌታ የቀረበ ራሱ አርፎ ሌሎችንም ያሳርፋል፡፡ እዳና ሸክም ከመሆን አልፎ ሌላም ነገር እዳና ሸክም እንዳይሆን ይከላከላል፡፡ ጥቅሙ እጥፍ ነው፡፡ በአንተም ሕይወት የሆነው ይሄው ነው፡፡ አንዳንዶቻችን ግን መነብነታችንን ስለማናውቅ እስካሁን እኛም አላረፍን፣ ሰዎችንም አላሳረፍን፡፡ ሌሎቻችን ደግሞ ወደጌታ መቅረብ ስለማንፈልግ ሸባነታችንን ታቅፈን የሰው ሸክም ሆነን እንኖራለን፡፡ አይበቃም?

ለ. አልጋው ለሰውየው በታመመ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በጤንነቱ ወቅትም ያገለግለዋል፤ ተሸክሞት የሄደውም ለዚህ ነው፡፡ ልክ በዚህ ዘመን ሸባዎች ሲፈወሱ ምርኩዛቸውን በመወርወር፣ የውስጥ ደዌ በሽተኞች ደግሞ መድሃኒታቸውን በመጣል መዳናቸውን እንደሚገልጹት እንደነሱ አላደረገም፡፡ አልጋውን በስሜታዊነት አልሰበረም ወይም አልጣለም፡፡ ምክንያቱም ህመሙና አልጋው ልዩ ቁርኝት የላቸውም፡፡ በህመም ወቅት የሚያገለግለው አልጋ በጤነኝነት ወቅት ተሰርቶ ሲያገለግል የነበረው ነው፡፡

ስለዚህ እኛም አንዳንድ ነገሮችን ከአንድ ወቅት መጥፎ አጋጣሚና መከራ ጋር ብቻ አያይዘን ዘለቄታዊ ጥቅማቸውን እንዳናጣ መጠንቀቅ አለብን፡፡

ስለዚህ የእግዚአብሄር ሰዎች ሆይ፡- መጽሀፍ ቅዱሳችንን ስናነብብ ማንበብ ያለብን ሲሰበክ በሰማነው መሰረት ሳይሆን አዲስ ነገሮችን ለማወቅ በሚጓጓ ክፍትና በመንፈስ ቅዱስ በታደሰ አእምሮ በመሆንና እያንዳንዷን ቁጥር ትኩረት ሰጥተን በተለያየ አቅጣጫ ለመመመዘን በመዘጋጀት ሊሆን ይገባል፡፡

የቤርያ ቁጥር 10 ጥያቄዎች መልሶች

1. ሚል 1፡6
2. በጳውሎስ እስራት ላይ መከራ ሊያስጨምሩበት (ፊል 1፡15-17)
3. ከእነሱ ጋር ጸንተው አለመኖራቸው (1ዮሀ 2፡19)
4. አንድ - ሳሙኤል (መጽሃፈ መሳፍንት)
5. ለ ሀሰት

አዘጋጅ - አበበ መንሻ (ዶ/ር)
ስ.ቁ. – 0936669160 ኢሜይል - abebe.meng@gmail.com
ፌስቡክ ገጽ - Berea teaching
ቴሌግራም https://t.me/bereamagazineethiopia

መጽሄቱን በኢሜይል በመላክ እና ኮፒ አድርገው በማደል ሌሎች ሰዎችም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
የቀድሞ እትሞችን በቴሌግራም ቻነል ላይ ያገኛሉ፡፡

የቤርያ ጥያቄዎች

1. ሰለሞን በመጽሀፈ መክብብ ውስጥ አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ብሎ ሁለት የመሆንን ጥቅሞች ይጠቅሳል፡፡ ከነዚህ ጥቅሞች መካከል አንዱን ጥቀስ፡፡
2. ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ያየው መቼ ነው?
3. ሱራፌል ስንት ክንፍ አላቸው?
4. በገላትያ መጽሀፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመንፈስ ፍሬዎች ስንት ናቸው? ስማቸውስ?
5. በጉ ሰባተኛውን ማህተም በፈታ ጊዜ ምን ተፈጠረ?

መልሱን በቁጥር 12 ላይ ያገኛሉ፡፡